24ኛ ዓመት ቁጥር 7
24th Year No. 7

ባሕር ዳር መጋቢት 22 ቀን 2011 ዓ.ም
Bahir Dar, March 31, 2019

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

**Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State**

*1324*
ያንዱ ዋጋ 45 ብር
Unit Price Birr 45.

## ማውጫ

***አዋጅ ቁጥር 257/2010 ዓ.ም***
***በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ2011 በጀት አመትን ለማጽደቅና የበጀት አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ***

## Content

**Proclamation No. 257/2018**
**In the Amhara National Regional State The 2018/19 Fiscal Year Suplementary Budget of Government Works Implementation Approval Proclamation**

## *አዋጅ ቁጥር 257/2010 ዓ.ም*

## *በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ2011 በጀት አመትን ለማጽደቅና የበጀት አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሠ) መሠረት ክልሎች የራሣቸውን በጀት ለማጽደቅና ሥራ ላይ ለማዋል በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት በ2011 የበጀት ዓመት የክልሉ መንግሥት ለሚያከናውናቸው ሥራዎችና ለሚያበረክታቸው አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት ማጽደቅና በሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

## Proclamation No. 257/2018

## A Proclamation Issued to Approve the 2018/19 Fiscal Year and Determine its Administration in the Amhara National Regional State of Government Works Implementation.

WHEREAS, it is found necessary to approve and implement the budgetary appropriations required for the activities to be done and services to be rendered in the 2018/19 Fisical Year, pursuant to the power vested in under Article 52 Sub-article 2 (e) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, to appropriate their own budget and implement it;

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የፌደራሉን መንግሥትና የክልሎችን የጋራ ገቢ ክፍፍል እንዲሁም የፌደራሉ መንግሥት ለክልሎች የሚሰጠውን ድጐማ በተመለከተ የፌደሬሽን ምክር ቤት የወሰነውንና የክልሉን የተለያዩ ታሣቢዎች መሠረት በማድረግ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን የ2011 በጀት ማወጅ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is needed to proclaim the 2018/19 budget of the National Regional State, in accordance with the decision of the House of Federation and the Region's various aspects concerning their common revenue appropriations of the Federal Government and the Regional States as well as the subsidy that the Federal State gives to the States pursuant to Article 62 sub- article 7 (e) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) እና (10) ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል፡፡

NOW, THEREFORE, the Amhara Nationa Regional State Council, pursuant to its pwer vested in the region's revised constitution Article 49, sub-article 3(1) and (10) provisions, has proclaimed the following:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## PART ONE
## GENERAL

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የ2011 በጀት ዓመት በጀት ማፅደቂያና አስተዳደሩን መወሰኛ አዋጅ ቁጥር257/ 2010 ዓ.ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State, the 2018/19 Fisical Year Budget Approval and Its Determination Proclamation No.256/2019."

## 2. ለ2011 የበጀት ዓመት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስራዎች ማስፈጸሚያ የተመደበ አጠቃላይ በጀት፡-

ከሐምሌ 1/2010 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2011 ዓ.ም. ባለው የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከፌደራል መንግሥት ድጎማና ከክልሉ ከሚገኘው ገቢ፦

**ገቢ………………… 43,538,755,109**

1 **ከመንግሥት ግምጃ ቤት:-** 40,076,684,508

ሀ/ በክልሉ የሚሰበሰብ መደበኛ ገቢ:- 10,500,000,000

- ከታክስ ገቢ:- 9,649,452,478
- ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች 850,547,522

ለ/ ከፌደራል መንግሥት መደበኛ የቀመር ጥቅል የድጋፍ በጀት:- 28,280,684,508

ሐ/ ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ:SDGs የፌደራል መንግሥት ድጋፍ:- 1,296,000,000

2. በክልሉ የሚሰበሰብ የውስጥ ገቢ:- 1,802,556,921

1. የከተሞች አገልግሎት ገቢ:- 1,500,000,000

2. ከውጭ አገር ዕርዳታ:- 159,513,680

ጠቅላላ የክልሉ የዘመኑ የበጀት ጣሪያ ብር 43,538,755,109

(አርባ ሶስት ቢሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ አንድ መቶ ዘጠኝ ብር) ከዚህ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ውስጥ በተጠቀሱት ስራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ የተመለከተው በጀት ተመድቧል፡፡



## 2. The Total Budget appropriated for the 2018/19 Fisical Year of the Amhara National Regional State:

Commencing from July 8, 2018 to June 30, 2019 Fisical Year, from the Federal State Subsidy and and the Region's Internal Revenue:

I. Revenue……………43,538,755,109

1. From Govenrment Treasury…40,076,684,508
   A. Recurrent revenue to be collected in the region…10,500,000,000
      - From tax revenue…9,649,452,478
      - From non-tax revenues…850,547,522
   B. Recurrent formula general subsidy from the federal government…28,280,684,508
   C. The federal government subsidy for the implementation of sustainable development goals (SDGs)…1,296,000,000
2. Internal revenue to be collected in the region…1,802,556,921
   1. The revenue of cities' service…1,500,000,000
   2. Aid from foreign countries…159,513,680

**Total ceiling of the Regional State Fisical Year Budget Birr…43,538,755,109** (Fourty-three Billion, Five Hundred Thirty-eight Million, Seven Hundred Fifty-five Thousand, One Hundred Nine Birr) is appropriated for the works and services mentioned herewith as follows:

**II.ወጭ** ……………………..........43,538,755,109

ሀ. ከመንግሥት ግምጃ ቤት:......40,076,684,508

1. ለቢሮዎች መደበኛና ካፒታል ሥራዎች:-…………….7,868,580,000
   - መደበኛ:-………….6,032,146,000
   - ካፒታል:-………….1,836,434,000
2. ለወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ለብሔረሰብ ም/ቤቶች የቀመር ጥቅል ድጋፍ…..…...…23,879,540,000
   - ➢ ለገጠር ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች (በብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ስር ያሉ ወረዳዎችንና ከተማ አስተዳደሮችን ሳይጨምር):-……..20,584,344,656
   - ➢ ለብሔረሰብ ምክር ቤቶች (በብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ስር ያሉ ዞን መምሪያዎችን፤ ወረዳዎችንና ከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ):- 3,295,195,344

3\. ለ8ኛ፣ 10ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ማስፈተኛ:- 117,653,000

4\. ለትምህርት ቤቶች መጽሐፍት ህትመት:- ….....40,000,000

5\. ለጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች የሠው መድኃኒት ግዥ:-………183,299,000

6\. ለመስኖ ልማት ግንባታ:-………………450,000,000

7\. ለገጠር መንገዶች ግንባታ:-……………1,000,000,000

8\. ለማሽነሪ ግዥ:-………………… 150,000,000

9\. በዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ በጀት ለተጀመሩ ነባር ፕሮጀክቶች ማስጨረሻ :-……1,600,000,000

10\. ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ መቀናጃ በጀት:- …355,910,000

**II. Expenditure…43,538,755,109**

A. From Government Treasury…40,076,684,508

1. Recurrent and capital works for Bureaus…7,868,580,000
   - Recurrent…6,032,146,000
   - Capital…1,836,434,000
2. **The Formula General Subsidy for Weredas, City Administrations and National Councils**…23,879,540,000

- ➢ For rural weredas and city administrations (excluding weredas and city administrations found under nationality administrations)…20,584,344,656
- ➢ For Nationality councils (zone departments including weredas and city administrations found under nationality administration zone)…3,295,195,344

3. For Examination of Grades 8,10 and 12…………………..117,653,000
4. Publication of Books for schools…40,000,000
5. Human Medicine Procurement for Health Centers and Hospitals…183,299,000
6. Building for Irrigation Development…450,000,000
7. Construction for Rural Roads…1,000,000,000
8. Procurement for Machinery…150,000,000
9. For Completion of Existing Projects Commenced by the Budget for Sustainable Development Goals…1,600,000,000
10. Integration Budget for Implementing Various Projects…355,910,000

11. ለንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ:- …250,000,000
12. ለአላማ ፈጻሚ ባለሙያዎች ቅጥር………200,000,000
13. ለኢንዱስትሪ ልማት ማስፋፊያ……200,000,000
14. ለልማት ድርጅቶች የማቋቋሚያ ድጋፍ….75,000,000
15. በልማት ወደ ኃላ ለቀሩ አካባቢዎች ለሚቀረጹ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ:-…200,000,000
16. ለአበባ እርሻ ልማት መሬት ካሳ ክፍያ እና መሰረተ ልማት ማስፋፊያ…… 525,000,000
17. ለከተሞች ልማት ድጋፍ:-….726,000,000
18. ለተሽከርካሪ ግዥ:-………100,000,000
19. ለተጨማሪ እሴት ታክስና ለቀረጥ ክፍያ:-… 75,000,000
20. ለክልል አቅም ግንባታ ማስፈጸሚያ…150,000,000
21. ለዘላቂ ልማት ማስፈጸሚያ:-………1,296,000,000
22. የክልሉ መጠባበቂያ:-……….. 634,702,508

**ለ/ የውስጥ ገቢ:-…………1,802,556,921**

1. ትምህርት ቢሮ (ከመምህራን ትምህርት ኮሌጅ):-…… 138,222,918
2. ጤና ቢሮ (ከሆስፒታሎች፣ ጤና ሳይንስ ኮሌጆች፣ ለጤና ጣቢያዎችና ሪጅናል ላብራቶሪዎች):-……… 1,146,765,597
3. ቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ:-………… 298,049,438
4. አማራ ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ፡-…14,000,000
5. ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን፡- ……60,193,082
6. ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፡-….4,150,000

11. Implementation for projects of potable water…250,000,000
12. Employment for Objective Implementer Professionals…200,000,000
13. For Expansion of Industry Development…200,000,000
14. Establishment support for Development Organizations…75,000,000
15. Implementation of Projects to be designed for Backward Areas in Development…200,000,000
16. Land Compensation for Flower Farming Development and Expansion of Infrustructures…525,000,000
17. Special support for Urbans Development…726,000,000
18. Procurrement for Vehicles…100,000,000
19. Payment for Value Added Tax and Customs…75,000,000
20. Implementation of Capacity Building for Region…150,000,000
21. Implementation for Sustainable Development…1,296,000,000
22. Contingency Budget for the Region…634,702,508

B. **Internal Revenue…1,802,556,921**

1. Education Bureau (from Teachers Education College)…138,222,918
2. Health Bureau (from Hospitals, Health Science Colleges, Health Centers and Regional Laboratories )…1,146,765,597
3. Technique, Vocational and Enterprises Development Bureau…298,049,438
4. Amhara Rural Roads Construction Agency…14,000,000
5. Correction Centers Administrations Commission…60,193,082
6. Agricultural Research Institute…4,150,000

7. ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ:- 1,955,236
8. የሙያ ብቃት ምዘና እና ማረጋገጫ ኤጀንሲ:- 13,000,000
9. ብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ:- 100,000,000
10. እፅዋት ዘርና ሌሎች የግብርና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ኳራንታይን ባለሥልጣን:-... 802,000
11. አመራር አካዳሚ፡-... 25,418,650

ሐ. የከተሞች አገልግሎት ገቢ፡.....1,500,000,000

መ. ከውጭ አገር ዕርዳታ፡-...159,513,680

- ለቢሮዎች፡-77,658,368
- ለወረዳዎች፡-.81,855,312

## ክፍል ሁለት
## የበጀት አስተዳደር

### 3. በጀቱ ስለሚስተዳደርበት ህግ-

የክልሉ የበጀት አስተዳደር የሚመራው በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት በተሻሻለው የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በወጡ መመሪያዎችና የአሠራር ሥርዓቶች መሠረት ይሆናል፡፡

### 4. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ቤት ስለሚኖረው በጀት የማስተዳደር ስልጣን፤-

በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት በተሻሻለው የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 ዓ.ም. አንቀፅ 18 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ ላይ ላልተመለከቱ ለአዲስ ወይም በበጀት ዓመቱ ለተፈቀዱ ለካፒታልም ይሁን ለመደበኛ ሥራዎች ከውጭ ብድር፣ ከዕርዳታ ወይም ከሀገር ውስጥ ብድር፣ ዕርዳታ ወይም ከሌላ ምንጭ ተጨማሪ ገቢ ሲገኝ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እየተወሰነ በሥራ ላይ እንዲውል ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሲሰበሰብ ለበጀት ዓመቱ በተጨማሪ በጀትነት እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡

7. Labor and social Affairs Bureau…1,955,236
8. Professional Quality Assessment and Assurance Agency…13,000,000
9. Mass Media Agency…100,000,000
10. Plant, Seed and other Agricultural Inputs Quality Control Quarantine Authority…802,000
11. Leadershi Academy…25,418,650

C. Revenue of Urbans' Service…1,500,000,000

D. Aid from Foreign countries…159,513,680

- For Bureaus…77,658,368
- For Weredas…81,855,312

## PART TWO
## BUDGET ADMINISTRATION

### 3. Administration Law of the Budget

The region's budget administration shall be based on the Revised Finance Administration Proclamation No. 178/2011 of the Amhara National Regional State and Issued Directives and Working Procedures of Finance and Economy Cooperative Bureau.

### 4. Budget Administration Power of the Council of the Regional Administration

Without prejudice to the provision of Article 18 of the Amhara National Regional State Budget Administration Proclamation No.178/2011, the council of the regional Government Administration shall decide and implement when additional income is gained from foreign loan, from aid or domestic loan, aid or from other source for new activities unspecified in the proclamation hereof, or for other capital and recurrent activites approved in the fisical year, causing to be approved by the Regional Council as a Suplementary Budget when holding its session.

## 5. የብሄራዊ ክልሉ አስፈጻሚ አካላት በጀት የማስተዳደር ስልጣን፡-

ሀ. የአማራ ብሔራዊ ክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ለየሥራ ክፍሎቻቸውና ፕሮጀክቶቻቸው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት የማስተዳደር ሥልጣን አላቸው፡፡

ለ. በዞን ደረጃ ምክር ቤት ያላቸው የብሔረሰብ አስተዳደሮች ለዞን፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች በዚህ የበጀት አዋጅ የተሰጣቸውን የበጀት ጣሪያ መሠረት በማድረግ በጀቱን የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን አላቸው፡፡

ሐ. የወረዳና ከተማ አስተዳደሮች በዚህ የበጀት አዋጅ የተሰጠውን የበጀት ጣሪያ መሠረት በማድረግ በጀቱን የማስተዳደር ሙሉ ስልጣን አላቸው፡፡

መ. በየደረጃው የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ ከተፈቀደላቸው በጀት ክፍያ እንዲፈፀምላቸው በሚጠይቁበት ጊዜ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ኃላፊ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል በዚህ አዋጅ መሠረት ታዟል፡፡

## 6. የወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ገቢን የማስተዳደር ስልጣን፡-

ከባህር ዳር፣ ጎንደርና ደሴ ከተማ አስተዳደሮች ውጪ ላሉ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች በበጀት ክፍፍል ወቅት በቀመር የደረሣቸው የመንግሥት ግምጃ ቤት ጥቅል በጀት በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ የሚሰበሰበውን የመደበኛ ገቢና ከክልሉ መንግሥት የሚላከውን ድጋፍ ያጠቃልላል፣ ባህር ዳር፣ ጎንደርና ደሴ ከተማ አስተዳደሮች የቀመር ጥቅል ድርሻቸው የወጪ ድጋፍ ሙሉ በሙሉ ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ የሚላክላቸው ይሆናል፡፡

## 5. Budget Administration Power of the Executive Organs of the National Region

**A.** The Heads of the Government Offices of the Amhara National Regional State are hereby authorized to administer the budget appropriated, pursuant to this proclamation, for the services of their respective departments and projects.

**B.** Nationality administrations having a council at the Zonal level are hereby fully authorized to administer the budget based on the budget ceiling allocated to the zone, wereda and city administrations by this proclamation.

**C.** Wereda and City administrations are hereby fully authorized to administer the budget based on the budget ceiling allocated to it by this proclamation.

**D.** When Executive Organs of all level require disbursement from the budget allocated to them, the Head of Finance and Economic Cooperative Bureau is hereby ordered, pursuant to this proclamation, to be disbursed from the National Regional State Revenue and other sources.

## 6. Authority to Administer Revenue of Weredas and City Administrations

The state treasury total budget appropriated for the weredas and city administrations, except Bahir Dar, Dessie and Gonder City Administrations, during budget allocation, shall include the regular revenue collcted by the wereda or city administration and the subsidy budget provided by the Regional Government; the expenditure support of their formula general share for Bahir Dar, Dessie and Gonder shall be completely send by the Finance and Economic Cooperative Bureau of the region.

ሀ. በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ይሰበሰባል ተብሎ ከሚታሰበው የመደበኛ ገቢ ዕቅድ በላይ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ/ም በሚሰበስቡበት ጊዜ በበጀት ዓመቱ ከእቅድ በላይ ከተሰበሰበው ገቢ 50 ከመቶውን በ2012 በጀት ዓመት ወረዳው ወይም ከተማ አስተዳደሩ በተጨማሪ በጀትነት የሚጠቀምበት ይሆናል፣

ለ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ "ሀ" በተመለከተው መሰረት ወረዳው በ2011 በጀት ዓመት ከእቅድ በላይ ከሰበሰበው መደበኛ ገቢ ውስጥ 50 ከመቶውን መጠቀም የሚቻለው ለምን ተግባር መዋል እንዳለበት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ሲፈቅድ በወረዳው ወይም በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት በ2012 በጀት ዓመት በተጨማሪ በጀትነት በማሳወጅ ይሆናል፣

ሐ. ወረዳው ወይም ከተማ አስተዳደሩ ከእቅድ በላይ ሰብስቦ በ2012 በጀት ዓመት እንዲጠቀምበት ተፈቅዶለት ስራ ላይ የሚያውለውንና በ2012 በጀት ዓመት በተጨማሪነት የሚታወጀውን የገንዘብ መጠንና የወጪ ዝርዝሩን ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ከሐምሌ 10 ቀን 2011 ዓ/ም በፊት ያቀርባል፤ እንዲሁም የክልሉን ድርሻ 50 ከመቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ትሬዠሪ ሂሳብ ፈሰስ ያደርጋል፣

A. Where weredas or city administrations collect recurrent revenue exceeding to their collecting plan until July 7, 2019, the revenue collected beyond plan of 50% shall be utilized by the Wereda or City Administration in the 2020 Fiscal Year being the the supplementary budget.

B. Based on this Article, sub-article (A), the wereda shall use the revenue of 50% that is collected beyond plan in the 2019 fiscal year by the wereda, when the Amhara Finance and Economic Cooperative Bureau allows for what purpose it is used causing to be proclaimed as the 2020 suplementary budget by the wereda or city administration council.

C. The Wereda or city administration shall submit the amount of money and expenditure particulars of the permitted money, collected beyond the plan, to use as the 2020 fisical year and the 2020 fiscal year that will be proclaimed additionally, to the finance and Economic Cooperative Bureau of the region before the date of 17th July 2018; as well as to submit the 50% share of the region to the treasury account of finance and economic cooperative bureau.

መ. በቀመር ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ከደረሣቸው የመንግሥት ግምጃ ቤት ጥቅል በጀት በላይ የመደበኛ ገቢ ለመሰብሰብ ያቀዱ ወረዳዎች ወይም የከተማ አስተዳደሮች በቀመር ድልድል ከመንግሥት ግምጃ ቤት የደረሳቸውን ጥቅል በጀት ያህል ከሚሰበስቡት የመደበኛ ገቢ የሚጠቀሙ ይሆናል፣ ወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች በቀመር ከደረሳቸው በላይ በእቅዱ እስከተመለከተው የገቢ እቅድ ድረስ የሚሰበሰቡት ገቢ የክልሉ ገቢ ይሆናል፣

ሠ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ "መ" የተመለከተው ተግባራዊ የሚሆነው ከባሕር ዳር፣ ጎንደርና ደሴ ከተማ አስተዳደሮች ውጪ ላሉት ሌሎች ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ሲሆን ባሕር ዳር፣ ጎንደርና ደሴ ከተማ አስተዳደሮች በ2011 በጀት ዓመት አቅደው የሚሰበስቡትን መደበኛ ገቢ ሙሉ በሙሉ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ትሬዠሪ ሂሳብ ፈሰስ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ከእቅድ በላይ በሚሰበስቡበት ጊዜ ግን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ "ሀ" መሰረት ተግባራዊ ይሆናል።

## 7. የበጀት ዝውውር ስልጣን፡-

ከዚህ በታች ለተመለከቱት አካላት በዚህ አዋጅ መሠረት የበጀት ዝውውር ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

D. Weredas and City Administrations, which plan to collect regular revenue beyond the state treasury total budget appropriated on the basis of grant formula, shall utilize the amount of revenue equivalent to the total budget appropriated to them from the state treasury on the basis of grant formula. The revenue collected by the weredas or city administrations which is beyond their share on the basis of formula upto the indicated revenue plan shall be the revenue of the region.

**E.** Whereas the indicated in this article, sub-article "D" is applied in other weredas and city administrations except Bahir Dar, Dessie and Gonder City Administrations, Bahir Dar, Dessie and Gonder shall completely submit their planned recurrent revenue in 2019 fiscal year to the region's finance and economic cooperative bureau tresasury account. But it is applied according to this article, sub-article "A" when they collect beyond plan.

## 7. Authority of Budget Transfer

The organs indicated below are given power to transfer budget pursuant to this proclamation:

**ሀ/ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ፡-**

1. ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደ የመደበኛ በጀት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት አስቀድሞ ለተፈቀደ ወይም ላልተፈቀደ መደበኛ ወይም ካፒታል በጀት፤
2. ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተፈቀደ የካፒታል በጀት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት አስቀድሞ ለተፈቀደ ወይም ላልተፈቀደ ካፒታል በጀት፤
3. በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መ/ቤት ሲጠይቅ ከመደበኛ በጀት ወደ ተፈቀደ ካፒታል ፕሮጀክት፣
4. በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ከአንድ ካፒታል ፕሮጀክት ወደ ሌላ አስቀድሞ የተፈቀደ ካፒታል ፕሮጀክት
5. በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ከአንድ የሥራ ክፍል ወደ ሌላ የሥራ ክፍል የማዛወር፣
6. በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ፣
7. በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ የሥራ ክፍል ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወርና

**A. <u>The Amhara National Regional State Finance and Economic Cooperative Bureau</u>**

1. From appropriations made for Recurrent Budget of a Government Office to Previously appropriated or non-appropriated Recurrent or Capial Budget of another Government Office;
2. From appropriations made for Capital Budget of a Government Office to previously appropriated or non-appropriated Capital Budget of another Government Office;
3. From Recurrent Budget to appropriated capital project upon the request of a Government Office at the Regional Level;
4. From One Capital project to another previously appropriated capital project upon the request of a Government Office at the Regional level;
5. From one Operational Department to another Operational Department upon the request of a Government Office at the Regional level;
6. From appropriations made for Salary and Allowance to Operational expenditure upon the request of a Government Office at the Regional level;
7. From One item of Expenditure to another item of Expenditure within one Operational Department upon the request of a Government Office at the Regional level; and

8. በክልል ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር ስልጣን አለው፡፡

**ለ.የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤቶች፡-**

1. አስተዳደሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአንድ የመንግሥት መ/ቤት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የማዛወር፣
2. የአስተዳደር ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአንድ የመንግሥት መ/ቤት መደበኛ በጀት በጀቱ ወደ ተያዘለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ካፒታል በጀት የማዛወር፣
3. የአስተዳድር ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአንድ የመንግሥት መ/ቤት ካፒታል በጀት ወደ ሌላ አስቀድሞ የተፈቀደ/ያልተፈቀደ ካፒታል በጀት የማዛወር፣
4. የአስተዳደር ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በወረዳና ከተማ አስተዳደሮች የተያዘን የመደበኛና የካፒታል በጀት በጀቱ በተፈቀደለት ወረዳና ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የጽሑፍ ስምምነት መሠረት ወደ ዞኑ ወይም ወደ ሌላ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የማዛወር ስልጣን አለው፡፡

8. From one item of Expenditure to another item of Expenditure within a project upon the request of a Government Office at the Regional level.

**B. <u>National Administrative Councils</u>**

1. To transfer from one Government Office to another Government Office where the Administration gets it necessary;
2. To transfer from Recurrent Budget of the Government Office to a Government Office from which the budget is allocated, or to the Capital Budget of another Government Office where the Administrative Council gets necessary;
3. To transfer from Capital Budget of the Government Office to another previously appropriated/ non-appropriated capital Budget where the Administrative Council finds necessary;
4. To transfer the Recurrent and Capital Budget allocated for the Wereda and city administrations to the Zone or another Wereda or city administrations in accordance with a written agreement made by the Wereda Administrative Council for which the Budget is appropriated where the Administrative finds it necessary.

## ሐ/ የብሔረሰብ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር መምሪያ፦

1. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት/ቅርንጫፍ ሲጠይቅ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ከአንድ የሥራ ክፍል ወደ ሌላ የሥራ ክፍል የማዛወር፣
2. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ሲጠይቅ በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥር ከአንድ ፕሮጀክት ወደ ሌላ የተፈቀደ ፕሮጀክት የማዛወር፣
3. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ለአንድ የሥራ ክፍል ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ የማዛወር፣
4. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ የሥራ ክፍል ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወርና
5. በዞን ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር ሥልጣን አለው፡፡

## C. Finance and Economic Cooperative Department of the National Administration

1. To transfer from One Operational Department to another Operational Department under the same Government Office upon the request of a government office /branch at the zonal level;
2. To transfer from one project to another appropriated project under the same Government Office upon the request of a Government Office Branch at the Zonal level;
3. To transfer from salaries and allowances appropriated for one Operational Department to Operational Expenditure upon the request of a Government Office at the Zonal level;
4. To transfer from one item of Expenditure to another item of expenditure within the same operational department upon the request of a Government Office at the Zonal level, and
5. Has a power to transfer from one item of Expenditure to another item of Expenditure within the same project where a Government Office at the Zone level requests.

## መ/ የወረዳና ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት፦

1. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በተፈቀደ የካፒታል በጀት ውስጥ ከአንድ ፕሮጀክት ወደ ሌላ ፕሮጀክት፣
2. የወረዳው ወይም ከተማው አስተዳደር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከመደበኛ በጀት ወደ ካፒታል ፕሮጀክት የማዛወር፣
3. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለአንድ የሥራ ክፍል ከተፈቀደ መደበኛና ካፒታል በጀት ወደ ሌላ አስቀድሞ የተፈቀደ/ያልተፈቀደ መደበኛና ካፒታል ፕሮጀክት የማዛወር፣
4. የወረዳው ወይም ከተማው አስተዳደር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የማዛወር ስልጣን አለው፡፡

## ሠ/ የወረዳና ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች

1. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ያለ የመንግሥት መስሪያ ቤት ሲጠይቅ ለአንድ የሥራ ክፍል ከተያዘው በጀት ወደ ሌላ የሥራ ክፍል፣

## D. The Wereda and City Administrative Council

1. To transfer from one project to another project within appropriated capital Budget where the Wereda or City Administration Office requests;
2. To transfer from Recurrent Budget to Capital Project where the Wereda or City Administrative Council finds necessary;
3. To transefer from Recurrent and capital Budget appropriated for one operational department to another previously appropriated/non-appropriated Recurrent and Capital Project where the Wereda or City Administrative Council finds necessary;
4. Has the power to transfer budget from a Government Office to another Government Office where the Wereda or City Administrative Council gets necessary.

## E. The Wereda and City Admimistration Finance and Economic Cooperative Offices

1. To transfer from Budget appropriated for one Operational Department to another Operational Department upon the request of a Government Office at the Wereda or city Administrtion level;

2. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደመወዝና አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ የማዛወር፣
3. በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ ፕሮጀክት ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር፣
4. በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ደረጃ ያለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲጠይቅ በአንድ የሥራ ክፍል ውስጥ ከአንድ የሂሣብ መደብ ወደ ሌላ የሂሣብ መደብ የማዛወር ሥልጣን አለው፡፡

### 8. በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ ስለማይውል በጀት

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/II/ሀ ስር የበጀት ድጋፍ የተደረገላቸው የክልል ቢሮዎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተሻሻለው የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 በአንቀፅ 36 ተራ ቁጥር 1 መሠረት በበጀት ዓመቱ የተፈቀደና ወጪ ሳይደረግ ወይም ሥራ ላይ ሳይውል የቀረ ሂሳብ ሁሉ ሥራ ላይ መዋሉ ቀርቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ የትሬዥሪ ሂሳብ ፈሰስ ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪም ስለአጠቃቀሙ ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ማቅረብ አለባቸው።

2. To transfer from appropriations of the Recurrent Budget allocated for salary and allowance to Operational Expenditure upon the request of a Government Office at the Wereda level;
3. To transfer from one item of Expenditure to another item of Expenditure within the same project upon the request of a Government Office at the Wereda or city Administrtion level;
4. Has the power to transfer from one item of Expenditure to another item of Expenditure within the same Operational Department upon the request of a Government Office at the Wereda or city Administrtion level.

### 8. <u>An Idle Budget of the Fiscal Year</u>

**A.** Subsidized Regional Bureaus, Zones, Weredas and City Administrations under Article II (A) of this proclamation, are required to send, pursuant to Article 36, sub-article 1 of the Amhara National Regional State Revised Finance Administration Proclamation No 178/2011, those appropriated but unused or unimplemented accounts within the fiscal year, to the treasury account of Finance and Economic Cooperative Bureau instead of implementing it for operations. In addition, they should submit monthly account report to Finance and Economic Cooperative Offices at all level.

## 9. የከተሞች ልማት ልዩ ድጋፍ አጠቃቀም

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/II/ሀ/ 17 ስር ልዩ ድጋፍ የተደረገላቸው የከተማ አስተዳደሮች የተሰጣቸውን ልዩ ድጋፍ ለተፈቀደው ተግባር ብቻ የማዋል ግዴታ አለባቸው፡፡ በጀቱን በአግባቡ ሥራ ላይ ያዋሉት ስለመሆኑ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ የመቆጣጠር ስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

ለ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/II/ሀ/ 17 ስር ለከተሞች ልማት ልዩ ድጋፍ ከተመደበው ብር 726,000,000 ተጠቃሚ የሆኑ ከተማ አስተዳደሮች የከተሞች የአካባቢ ልማት ኘሮግራም (ULGDP) ለታቀፉ ከተማ አስተዳደሮች መቀናጅ የሚታሰብ ሆኖ ይህም ክልሉ የሚያዋጣው የመቀናጅ በጀት ይሆናል፡፡

ሐ. የከተሞች ልማት ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ የሚሆኑ ከተማ አስተዳደሮች የሚደርሳቸውን በጀት መጠን ከከተማው አገልግሎት ገቢ የሚፈለግባቸውን ድርሻ ማዋጣት የሚጠበቅባቸው ሲሆን ዝርዝር አፈፃፀሙ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል።

## 9. Special Subsidy Usage of Urbans Development

A. Those Citiy Administrations, for which special subsidy is made for them under Article 2/ II (A) 17 of this proclamation, shall implement the subsidy only for the appropriated operations. So, the regional finance and economic cooperative bureau is given the power, in this proclamation, to control the proper implementation of same.

B. In accordance with Article 2/II/ (A) 17 of this proclamation, the beneficial city administrations from the allocated budget of 726,000,000 birr, the urbans environment program (ULGDP) shall be calculated from each share and shall be matching fund of the region.

C. The city Administrations that shall use special Support of urban developments have a responsibility to allocate their own budget share for the urban service Revenue. The particular implementation shall be determined by the Amhara Regional State Administration council.

## 10. የከተማ አገልግሎት ገቢ

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/II/ሐ/ የከተማ አገልግሎት ገቢ የሚሰበስቡ ከተሞች አጠቃቀምን አስመልክቶ የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 37/98 የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደርን መሰረት ያደረገ ይሆናል።

ለ. ከተሞቹ ይሰበስባሉ ተብሎ ከሚታሰበው የከተማ አገልግሎት ገቢ ዕቅድ በላይ በሚሰበስቡበት ጊዜ ከእቅድ በላይ የተሰበሰበው የከተማ አገልግሎት ገቢ በ2011 በጀት ዓመት ሥራ ላይ መዋሉ ቀርቶ በ2012 በጀት ዓመት የከተማ አገልግሎት ገቢው እቅድ አካል ሆኖ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/II/ሐ/ የከተማ አገልግሎት ገቢ ሰብስበው እንዲጠቀሙ የታወጀላቸው ከተሞች የበጀት አጠቃቀሙን አስመልክቶ በጀቱን ለምን ተግባር እንደሚያውሉት የሚገልፅ የድርጊት መርሃ ግብርና አፈፃፀሙንም በተመለከተ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ እና በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

## 10. City Service Revenue

A. In accordance with Article 2(II) (C) of this proclamation, the utilization revenue of cities that collect urban service shall be based on the Regional Administration Council's Regulation No. 37/2006 of the City Administrations and Municipalities Finance Administration.

B. When cities collect beyond the anticipated plan of city service collection, the city service revenue becomes the part of the 2020 fiscal year city service revenue plan instead of being used in the 2020 fiscal year.

C. In accordance with Article 2/II/ (C) of this proclamation, cities that have been proclaimed to use collecting urban servive revenue should prepare an action plan for what purpose they will use and its implementation and report to the Region's Finance and Economic Cooprerative bureau as well as to offices of Finance and Economic Cooperative at all levels.

## 11. የውስጥ ገቢ

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/II/ለ/ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 11 የውስጥ ገቢ እንዲጠቀሙ የታወጀላቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት አጠቃቀሙን አስመልክቶ የውስጥ ገቢ ሰብስበው እንዲጠቀሙ ሥራ ላይ የዋሉትን አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን መሰረት ያደረገ ይሆናል።

ለ. መሥሪያ ቤቶቹ ይሰበስባሉ ተብሎ ከሚታሰበው የውስጥ ገቢ ዕቅድ በላይ በሚሰበስቡበት ጊዜ ከእቅድ በላይ የተሰበሰበው የውስጥ ገቢ በ2011 በጀት ዓመት ሥራ ላይ መዋሉ ቀርቶ የ2012 በጀት ዓመት የውስጥ ገቢው እቅድ አካል ሆኖ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/II/ለ/ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 11 የውስጥ ገቢ የታወጀላቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት አጠቃቀሙን አስመልክቶ በጀቱን ለምን ተግባር እንደሚያውሉት የሚገልፅ የድርጊት መርሃ ግብርና አፈፃፀሙንም በተመለከተ ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ እና በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

## 11. Internal Revenue

A. Sectors that have been proclaimed to use the internal revenue pursuant to Article 2/II/ (B) from numbers 1 upto 11 of this proclamation, concerning the budget utilization, shall be based on the proclamations, regulations and directives being used to use collecting internal revenue.

B. When sectors collect beyond the anticipated plan of internal revenue collection, the collected revenue collected beyond the plan becomes the part of the the 2020 fiscal year internal revenue plan instead of being used in the 2019 fiscal year.

C. Sectors that have been proclaimed the internal revenue pursuant to Article 2/II/ (B) from numbers 1 upto 11 of this proclamation, concerning the budget utilization, should prepare an action plan for what purpose they will use and its implementation, and report to the Region's Finance and Economic Cooprerative bureau as well as to offices of Finance and Economic Cooperative at all levels.

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### 13. መመሪያ የማውጣት ስልጣን፡-

የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ለዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት የሚረዱትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 14. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፡-

ይህ አዋጅ ከሐምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባሕርዳር

ሐምሌ 1/2010 ዓ.ም

ገዱ አንዳርጋቸው

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 12. Inapplicable Laws

Any Law, regulation or directives inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters stated in this proclamation.

### 13. Power to Issue Directives

The Regional Finance and Economic Cooperative Bureau may issue detailed directives necessary for the implementation of this proclamation.

### 14. Effective Date of the Proclamation

This proclamation shall come into force as of the 8th day of July 2018.

**Done at Bahir Dar,**

**This 19th day of July 2018**
**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Regional state**